# <u>በምርጫ ወይስ በጡጫ</u>

ምከረው ምከረው እምቢ ሲል መከራ ይምከረው የተባለውን ሀቅነቱን ለመግለፅ ይሆናል በሚያሰኝ መንገድ ተቃዋሚ ድርጅቶች ነን የሚሉት ያለፈውን ስህተት መድገምን የመረጡ ይመስላል፡፡ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ የወያኔ ምርጫ ላም አለኝ በሰማይ መሆኑን ደም ገብሮና ተሰቃይቶ ያወቀው ሆኖ ሳለ መሪዎችህ ነን ነፃ ልናወጣህ ነን ባዮቹ ደግሞ በወያኔ የ 2002 ምርጫ ለመሳተፍ ከወዲሁ ደፋ ቀና እያሉ ናቸው፡፡ ማንኛውም ድርጅት ባመነበት መንጎድና ዋጋውንም በዚያው መቀበል መብቱ ቢሆንም ሕዝብን አሳስቶ ለፍዳ መዳረግ ደግሞ ይቅርታ የማይደረግለት ጉዳይ ነውና በዝምታ የሚታለፍ ሳይሆን ያቺ የማይወዷትን ግን ማንነታቸውን የምትገልፀውን ቅፅል ማለትም “ ሆዳምን” አከናንቦ ማለፉ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

ከግንቦት 97 ወዲህ በተካሄደው ባለፈው ዓመት የየይስሙላ ምርጫ ሕዝብ በምርጫ ቦታው ባለመገኘትም ሆነ ስድብ አዘል የምርጫ ወረቀቶችን በሳጥን በመጣል ተቃውሞውን ቢያሰማም ወያኔ አሸናፊ ነኝ ሕዝብ መረጠኝ ብሎ ተመፃድቆ በስልጣን መቀጠሉ አልቀረም፡፡ የወያኔ ምርጫ ዋጋ ቢስ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ እያወቀ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሌላ መንገድን በመሻት ፈንታ በወያኔ ፀረ ሕዝብ ቀልድ ተሳትፈው ለአረመኔው አገዛዝ ሽፋን ለመስጠት ሲረባረቡና ሲጠላለፉ ማየት መቸም ምፀት ነው፡፡ልዩ ልዩ ድርጅቶች በምርጫው ለመሳተፍ ተዘጋጅተናል ብለዋል፡፡ ማንም ባይጠራቸውም ወደ ሀገር ገብተን በዚሁ ቅሌት ተዋኒያን እንሆናለን ያሉ ሌሎችም አሉ፡፡ በቅርቡ ደግሞ አንድ የተቃዋሚ ድርጅት መሪ እንዳለው ጡረታቸውን ሊያስከብሩ ይሁን ሌላ ያላሳወቁ አዛውንት ስደተኞችና የቀድሞ የሆነ ድርጅት አባሎች ወደ አዲስ አበባ ነጉደዋል፡፡ እነዚያ ራሳቸውን አስታራቂ ሽማግሌዎች የሚሉ እጅ አስነሺና አስጎንባሽ ግለሰቦችም ተመላሾችንና መሰሎቻቸውን ከወያኔ እናደራድራለን ሲሉም ተደምጠዋል፡፡ ይህን አጋጣሚ በመጠቀምም የወያኔ አገዛዝ የሰላ አፈቀላጤ የሆነው ጋዜጣም የትጥቅ ትግል ስልት ጊዜ ያለፈበት መሆኑን ሊያሳምነን ወረቀት ጨርሷል፡

ወያኔ በስልጣን እስካለ የምርጫ አማራጭ፤ የሰላማዊ ትግል አማራጭ የማይሰሩ መሆናቸው ግልፅ ሆኗል፡፡ በህሊናውና በአንጎሉ ላይ ያልተኛ ሁሉ የሚገነዘበው ሀቅ ነው፡፡ ተጨባጩ ሁኔታ ሁለገብ ትግልን-- ብረት አንግቦ መነሳትን መሸፈት ማመፅን የግድ ይላል፡፡ ይህን አማራጭ የሚቃወሙት ክፍሎች አንድም ይህ ስልት ጊዜው አልፎበታል ሲሉ በሌላ በኩል ደግሞ በትጥቅ የመጣ በግድ ጨቋኝ ይሆናል፤ በትጥቅ ካልሆነ አይወርድም ብለው ይከራካራሉ፡፡ ከጹላ መላ ይሻላል ብለው ሰብከው በመላ ለወያኔ ያደሩት ሁሉ ሲለፍፉት የቆየው ይህንኑ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ትጥቅ ትግል ጊዜው ያለፈበት ስልት ሳይሆን በስራ እየዋለና ውጤትም እያመጣ ያለ ነው፡ በቅርቡ በኔፓል ስልጣን የያዘው የግራ ሀይል ለዚህ የበቃው በትጥቅ ትግል አማካኝነት ነው፡፡፡ በዳርፉር በአሜሪካ ሳይቀር የሚደገፉት ትጥቅ ትግል የሚያካሂዱ ናቸው፡፡ በቻድ ትጥቅ ትግል ይካሄዳል፡፡ በኮሎምቢያና ስሪ ላንካም እንዲሁ፡፡ በኮንጎም፡፡ በሰሜን ዩጋንዳ ወሮበላ የሆነ ይዘት

ያለው የትጥቅ ትግል ተካሂዶ አካሂያጁ ድርጅት ተከብሮና አድማጭ አግኝቶ ከመንግስት እየተ ደራደረ ነው:: በፊሊፒንስ፤ በታይላንድ በሚያንማር በርማ ትጥቅ ትግሎች ይካሄዳሉ:: አሜሪካም ሆኑ ምዕራቦቹ ባመቻቸው ይደግፋሉ:: ምዕራቦቹም ላይ በኢራቅና በአፍጋኒስታን የትጥቅ ትግል ይካሄዳል:: ወገን ለይቶ ይህ ሽብር ነው ይህ ሕዝባዊ ትግል ነው ማለትም ይቻላል ግን ስልቱ ያለና ሕዝቦችም እየተገለገሉበት ነው:: ሶማሊያስ ምን ሊባል ነው? በዚህ በዚያ ቢታይም አሜሪካ ካልደገፈን ትግል አይቻልም ብሎ እጅ መስጠት ደግሞ ከኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ አይደ ለም:: ይነስ ይብዛም በኢትዮጵያም ቢሆን ትጥቅ ትግል እየተካሄደ ነው:: ማለትም ፀረ ትጥቅ ትግል አቅዋም ትክክለኛ አለመሆኑንም ብዙ ተመክሮ እያሳየ ነው:: ለዚህም ነው የወያኔና አፈቀ ላጤዎቹ ትጥቅ ትግል ጊዜ አልፎበታል ልፈፋ ትጥቅ አስፈቺና ባርነትን ተቀበሉ ሰበካ ሆኖ የሚጋለጠው:: ወያኔ ደግሞ በትጥቅ ትግል ስልጣን የያዘ ዴሞክራሲያዊ አይሆንም ሲል ማሾፉ ነው ወይስ ግለሂስ በሎ መጠይቅም ይገባል? ዋናው የድርጅት ይዘትና ሕዝብም መብቱን ለማስከ በር ምን ያህል ዝግጁ ነው የሚለው ነው:: አንዱን አምባገነን በሌላ አላስተካም ማለት አለበት እንጂ ቅዠት ተፈርቶ እንዲሉ ገና ለገና በሚል ይህን ፀረ ኢትዮጵያ ዘረኛ ቡድን በጫንቃው ማቆየት የለበትም::

ይኸው የእኔንም ጉምድ ተባባሉ እጆቻቸውን በተራ ተራ ያስቀረጡ ሌቦቹ አሉ እንደሚባለው ይሆን እንደሁ እንጂ አንዱ ተለጣፊ በሌላው ጎዳና ሲተም መጨረሻው ያው ወያኔ ቆሻሻ ጫማ ስር መውደቅ መሆኑ አከራካሪ አይደለም:: የቂል ጓደኛ ቂል የተባለውንም ያልፋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ጦርነት ሰልችቶታል የሚለውን የወያኔ ቀረርቶ እያሰሙ (ሕዝብ ጭቆና ይበልጥ ያልመረ ረው ይመስል) ለወያኔ ተጎንብሶ መገዛትን፤ መቃወምን አለዝቦ በኤኮኖሚው መስክ መወራጨትን ና መሰል የአጅ መስጠት ጥሩምባ የነፉትና ብለውም ከባዕድ ሀገር ሳይቀር ወደ አዲስ አበባ የተ መለሱት ዛሬ የት እንደደረሱ መጠየቅ ይቻላል:: አንዳንዶቹ ሕዝብ ያፈረባቸው ተለጣፊዎች ሆነ ዋል:: ለወያኔ ያደረ ተለጣፊ ኢሕአፓ እንመሰርታለን ያሉት ደግሞ በሕዝብ ተተፍተው በወያኔ በራሱም ወግዱ ተብለው ውድቅ ሆነው ባክነው ቀርተዋል:: የኤኮኖሚ ትግል ያሉት ከትግሉም ከኤኮኖሚውም አሮባቸው ዳግም ስደት ተመልሰዋል:: በምርጫ ያሉትም ጡጫን አግኝተው ለኡ ኡታ ተዳርገዋል:: ወያኔ ለወዳጁ እሳት ይዟል በእጁ ከመሆን የተለየ ሁኔታ አልተከሰተም:: ታማኝ ተቃዋሚ ነን ያሉትም የሕዝብ መሳለቂያና የወያኔ መጫወቻ አሻንጉሊት እንደሆኑ አሉ:: ከወያኔ ጋር ማበርና በዘረኛው ፖለቲካበደኖና አሰቦትንም መውለድ ማበርከት ይቻላል ያሉትም ዛሬ ከሀገራቸው ተባረው የት እንዳሉ ምስጢር አይደለም::ይህ ግልፅ ሆኖ እያለ ዛሬ ከ 17 ዓመት የመከራ ተመክሮ በኋላ ለወያኔ ለማደር መኮልኮል የሚሉት ክፍሎች ጤና ለመሆናቸው ጥያቄ መቅረቡ ተገቢ ነው:: የአንድ ተቃዋሚ ተብዬ ድርጅት መሪ ፕሮፌሰር በቅርቡ እንዳለው ግለሰቦ ቹም ሆኑ ቡድኖቹ ተስፋ ቆርጠውና አርጅተው ምናልባትም ጡረታ ይገኝ ይሆን ነው ብንል ስህተት አይሆንም:: ቀቢፀ ተስፋ መጎንበስን ያስከትላል:: የሌባ ሞኝ ከጎተራ ስር ይገኝ አይደል? በ2002 ከወያኔ ጋር በምርጫ እንሳተፋለን ብሎ ደፍሮ መናገሩ ራሱ ሊያሳፍር ሲገባው ይባስ

ብለው ትጥቅ ትግል ወይም ሁለገብ ትግል ያሉትን ሊያወግዙና ሊወነጅሉ ሲነሱ ማዳመጥ መቸም የሌባ ዓይነ ደረቅ እንድንል ገፋፊ ነው፡፡ ይሉኝታና ሀፍረት ደግሞ ከአድርባዮች ጎራ ደብዛቸውም የለ ማለት እንችላላን፡፡

ከአድርባይነትና ሆዴ ይቅደም ባሻገር ደግሞ ዘንድሮ ፖለቲካ የሚባለውም ውሉ የጠፋቸው ብዙ መሆናቸውም መገንዘብ እንገደዳለን፡፡ ፖለቲካ ንግድ ያውም በአየር ባየሩ ዓይነት የመሰላቸው ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ለመርህ፣ለፅናት፣ ለሕዝብ ታማኝነት ና መሰል ፀጋዎችና ቅዱስ ዓላማዎች ባዳ የሆኑ ጮሌዎች እነ አበበ ቢቂላና ተከታዮቹ ድህነትን በሩጫ ካመለጡ እኛስ በፖለቲካ ለምን አንሞክርም ያሉ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ዘመኑ ፖለቲካ የመጡት አንዳንዶቹ ራሳቸውም ከበርቴ ሆነው መለስ ዜናዊ ቦዘኔ የሚለው የእኔ ብጤውን መነሳሳት የሚፈሩ ናቸውና ትግሉ የማያዛልቅ ፀሎት ዓይነት ሆኖባቸዋል፡፡ ፀንቶና ቆርጦ መገኘቱ የሚጠይቀውን ወኔም ሆነ መከራ ቻይነት በሩቁም ሊቃኙት ፍላጎት የላቸውምና ነጋ ጠባ ዕድል ባገኙበት አለና ለዕርቅ፣ አናግሩን እንጂ በማርያም፣ በአላህ ብለው ድርድር ፍለጋ ሲደፉ ማየት አይቀሬ ሆኗል፡፡ ለመስዋዕትነት የተነሳሳውን ሕዝብ ትግል እያኮላሹና እያሳፈሩ ተስፋ መቁረጥን ያራግባሉ፣ ፈለጉም አልፈለጉም በዚሁ ለወያኔ ይረዳሉ፡፡ በመሆኑም አርቆ ማሰብን፣ ለወሳኝ ፍልሚያ ቀበቶን ጠበቅ ማድረጉ ለተፈታ ሱሪያቸው የሚበጅ መስሎ አይታያቸውምና የቁጣ ቀስታቸው የሚሳበው ከሕዝብ ጎን ፀንተው በሚታገሉት ላይ ይሆናል፡፡ ግፋ ሲል ትግሉ እነሱ ሳብ ጎተትን ይሰብካሉ፡፡ ድፈር ሲባል ጠንቀቅን፣ተባበር ሲባል ክፍፍልን፣ ፋኖ ተሰማራ ሲባል ተራራ ወጥተን ሱባዔ እንግባን፣ ጠላትን ምታ ሲባል ጠላት የለንምን ይጮኻሉ፡፡ ካልሆነማ ታስረው ተቀፍድደው እያለ ከኢሕአዴግ ቅራኔ የለንም ብለው ይለፍፉ ነበር? ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር ነውና ማፈሪያችን ሆነዋል፡፡

ዛሬ ለወያኔ መጎንበስን ዋና ሰባኪዎች ተማርን አወቅን ባዮች ለመሆናቸው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ አያውቅም አልተማረም የተባለው ሕዝብማ ወዳጅ ጠላቱን ከለየ ውሎ አድሯል፡፡ ልጆቿን ለቀይ ሽብር ወንጀለኞች የገበረችው እናት፣ ልጆቿ በወያኔ የተፈጁባት እናት ጠላቷን ታውቃለች፡፡ማን ጠላት ማን ወዳጅ ለሚለው መልሱ በእሷ በደማ ልብና ከእንባዋ መሀል የሚገኝ ነው፡፡ ሌላውማ፣ በወሬማ እኔም አለኝ ቁስል ያንተን የሚመስል ከመሆኑ ሌላ እንዲያውም ይባስ ሆኖብንትላንት በወገኖቻችን ላይ ቀይ ትርዒት የሚሉትን ያሳዩት-- የፈፀሙት ዛሬ የታጋይና ሀገር ወዳደን ካባ ለብሰው በሰለባቸው ላይ ሲሳለቁ ማየት ተገደናል፡፡ የቀይ ሽብር ወንጀለኞችና የወያኔ ነፍሰ ገዳዮች በተጨባጭ ገጥመው የታገሉትና ሊታገሉ የሚችሉትንም ለማውደም በየፊናቸውና በትብብርም ሲሰሩ እያየን ነው፡፡ የወቅቱ ዋና ትኩረታችን በዋና ጠላት ላይ ነው በሚል የትላንቱን ወደ ጎን ትተን ትብብርን ብንፈልግም ከመግፋት ይሻላል መገፋት የተባለውን በአሉታዊ ተርጉመው ያልሻረ ቁስልን እያደሙ በሰማዕት እየቀለዱ ወደ ሌላ ትግል ይጋብዛሉ፡፡ ይህ ትግልን የሚጎዳ ሀላፊነትና ንሰሀ ፈላጊነት የጎደለው ሂደት መሆኑ መቸም ለማንም ግልፅ ሊሆን በተገባው ነበር፡፡

ታሪክን መርሳት ባይገባም የታሪክ ትዝታችን ከህቅ መጣላት የለበትም:: በሌላ በኩል ደግሞ ቅርስ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ያለፈ ክረምት ነውና ፤ ምናልባትም የአንጹ ፀሐይ ንጉስ ለሌላው ጨለማ የነበር ሊሆን ይችላልና ባለፈው ላይ ጎዝጉዞ መተኛቱ አይጠቅምም:: ሁሉም ትውልድ የራሱን ታሪክ እየፃፈ ማለፍ መቻል አለበት:: ደሙን ለሀገር ያፈሰሰውን ትውልድ ሁሉ መዘከር ሲገባን የሕዝብ ደም ያፈሰሰውን ደግሞ ጭራቅነቱን ማድበስበስ አይኖርብንም:: የእናት ጡት ነካሽ ዓይነቶች ግን በዘመናቸው ታሪክ ሊፅፉ ቀርቶ ጀግና ትውልድ ታሪክን ባፈተተችው እንጻ ትሄድ ይዞ ሲያስገብራት በቦታውም ያልነበሩ በሙት ወቃሽነት ተሰማርተው ሌት ተቀን ክሳቸው ን በትውልድና በታገሉ በተሰዉት ላይ ይደረድራሉ:: መታገልና መሰዋትንም በሞኝነት ፈርጀው፤ በባርነትም ቢሆን በመበርከት ከሞት ይሻላልን ስለሚያናፍሱ መጪው ትውልድ የትግሉ ነው ሕይወቴን ትቶ አሜሪካ ቤቴ እንዲል ይህ ነው የማይባል አስተዋፅዖን አድርገዋል:: ጀግኖቿን የማታከብር፤ የማትዘክር ሀገር ጀግኖች አታፈራምና ነው:: የተካሄደውን ፀረ ደርግ ትግል ሁሉ በስህተት በመፈረጅ የሚያወግዙት ጥሩ ቀንን ፍለጋ ወደ ጥንቱ መጓዝን ተገደዋል:: ያ የጥንቱ ግን ለስንቱ ደስታ ለስንቱ ደግሞ የመከራ ዘመን እንደነበር የምናውቀው ነው::

በሕዝብ ላይ ሳይጋበዝ የተጫነውን ወያኔ የተባለ አጋንንት ለማርገፍ ከትግል ውጪ መፍትሄ የለውም:: ኖሮ በነበር መራራ ትግልን ካልመረጥኩ የሚል አይገኝም ነበር:: በተለይ የትግልን ውጣ ውረድ ፤ስቃዩን ያወቁት ቀልል ያለ መንገድ ካገኙ እምቢም አይሉም:: ግን ሌላ መንገድ የለም:: በይኖራልና ይሞከር በ97 ለምርጫ ተገብቶ--ያውም የምርጫው ህግና ኮሚሽን በወያኔ ቁጥጥር ባለበት-- የተገኘውን ድል ወያኔ በጉልበት ቀምቶ፤ ንፁህንን ገድሎ፤አስሮና አግዞ እነሆ በአምባገነንነት ቀጥሏል:: መቀጠል ብቻ አይደለም ኢትዮጵያን ለአንዴም ለሁሌም ለማሽመድመ ድ በሁሉም መስክ እየዳከረ ነው:: አያሌ ወጣቶች ተደብድበዋል፤ተገድለዋል፤ታስረውም በመሰቃ የት ላይም ናቸው:: ታዲያ የመለስ መንጋ የት ላይ ተቀይሮ ነው ለድርድርና ለመተቃቀፍ የሚ ታጨው? በግለሰብ ደረጃም ቢሆን የመለስና ስብሀት ነጋ ፀረ ኢትዮጵያነት ሊበርድ የሚችል አይደለም:: የይስሙላ መድብለ ፓርቲውም የበዛ ሆኖ የወያኔ ቁንጮ የአንድ ፓርቲ ስርዓትን እያቀነቀነ ነው:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ወያኔ በድሎታል፤ ጎድቶታል፤እያደቀቀና ታይቶ በማይታ ወቅ ደረጃም እያሰቃየው ነው:: ቀለበት መንገድ ተሰራ፤ ሕንፃዎች ተገነቡ፤ ወዘተ በሚል የሚፈነድቁት ጥቂቶችና ፍዳቸውን እያዩ ያሉት ሚሊዮኖች የአንድ ሀገር ዜጎች ናቸው ለማለት በሚያስቸግር ደረጃ ደርሰናል:: ተማረ አወቀ የተባለውም በሞላም ባይሆን በተወሰነ ደረጃ ያስተማረውን ሕዝብ መታደግን ትቶ መሬት ልመራ፤ፎቅ ልስራ፤ጠጋ ብዬ ልነግድ፤ ሰልጠን ልበልና  ለወያኔ ልጎንበስ፤ገንዘብ ልሰብስብ፤ልሾም ወዘተ እያለ  ለወያኔ መቀለጃ መሆኑ ደግሞ የሚካድ አይደለም:: ተማርን አወቅን፤መጠቅን ሰለጠንን የሚሉት የፈረንጅ ቅፅላቸውን በማስፈራ ሪያ ከፊታችን እየደቀኑ፤ ለፖለቲካው ይፈይድ ይመስል ዶክተር፤ኢንጂኔር፤ ሲቪል መህንዲስ ፕሮፌሰር ወዘተ እያሉና ረጋ እንበል ሲባሉ ደግሞ በፀረ ምሁርነት እየከሰሱን፤ አለና አልበቃ

ብሏቸው ዋትስ አፕ፤አክችዋሊ፤ ዲሴማ፤ፐራክሲስ፤ፓራዳይም ወዘተን እየደነቁረብን፤ ሳይታገሉ ትግል ሰለቸንን እየለፈፉ፤ ከእኛ በላይ አዋቂ ለአሳርን በአድንቁን የምንለውን ተቀበሉን አጅበው ፤የተማረ ይግደላችሁን በላያችን ሊጭኑ ሲሞክሩ መታዘብም የግድ ሆኗል። የታገለውና የሚታገለውንማ መች ወደውት!

ያለፈው ትውልድ ምሁር ራሱን የሰርቶ አደሩ ወታደርና የጭቁኑ ሕዝብ ታማኝ አገልጋይ አድር ጎ የወሰደ ነበር። ሕዝቡን አግልግል ነበር መመሪያው። ዛሬ ደግሞ ይህ ተገልብጦ ራሳቸውን ልሂቅና ሁሉን አዋቂ ብለው የሰየሙ ተገብዘው መድረኩን በመያዛቸው ሕዝብን የመናቁ አቅዋም ም አለሁ አለሁ ብሎ ፖለቲካን ብልሽሽት ሊያደርግ ተውገርግሯል። የሕዝብ መሪዎች ነን ብለው ራሳቸውን የሾሙት ልንመራው ነው ያሉትን ሕዝብ ይዞታ ሆነ የትግል ታሪኩንም የማያውቁ ሆነዋል። የስቃዩ ተካፋይ መሆን ይቅርና ብሶቱም የሩቅ ሩቅ ወሬ ነው። የአንዳንዶቹ ውሎአቸው ከወያኔ መሪዎች እንጂ ከሚሰቃየውና ከታረዘው ሕዝብ ጋር አይደለም። ሌሎቹ ደግሞ በሩቅ ርቀት የሕዝብ ብሶት ገባን ቢሉም አኗኗራቸውም ሆነ የቁርጥ ቀን ልባቸው ከሕዝብ ጎን መቆምን አይፈቅድላቸውም። ትግል ብሎ ተጨባጩ ሁኔታ የሚጠይቀውን ትግል መሸሹ ከዚህም ይያዛል። ትጥቅ ትግል ወይም ሁለገብ የተባለውም ቢሆን ከምቾት ኑሮ መፈናቀልን በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ጠያቂ በመሆን ተፈላጊ አይደለም። እንደተባለውም አንዳንዶች ደግሞ ዕድሜ ይገፋና፤ ድል ደግሞ ይርቅና፤ ፅናት ደግሞ ይጫጫና የሰበብ ያለህ የማጠየቂያ ብለው ከወያኔ አገዛዝ ጋር ጠጋ ጠጋን ይመርጣሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ምኑ የቆሰለ ውሻ እንደልቡ አይጮህም ነውና ንግዴ ፋብሪካዬ፤የዶሮ ርቢዬ፤ሆቴሌ ጥቅሜ እንዳይነካ የሚሉ ደግሞ ጠባይ ማሳመራቸው የግድ ነው። ከተቃውሞው ለዘብ ማለት ይኖርባቸዋል።ከሁሉም ባሻገር ንብረታቸ ውንም ሊያጡ ይችላሉና ነው። ከበላህ ብላ ከሰው አትጣላ ይባል አይደል በነሱ? አድርባይነት ክህደት ቡከንነት ባንዳነት የምንለውን እኛ እነሱ መለዘብ፤መሰልጠን፤ መቻቻል፤ መኖረ መበርከት ይሉታል።

ሕዝብን ማዳመጥ ቢኖር ኖሮ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁሉም መንገድ ወያኔን ታግላችሁ ታግለን እናውድም ባይ ነው። ከሰርቶ አደሩ ቆርፋዳ እጅና መዳፍ ውስጥ ሀቅ ትገኛለች-- የሚፈልጋት ካለ ። ልጆቿን ለፋሺስትና ጠባብ አውሬዎች የገበረች እናት የታሪክና የሀቅ ባለቤት ናት። ሰርቶ አደሩ ሕዝብ ለሀገር የሚበጀውን መንገድ ያውቃል። በየገጠሩ መከራ እየተቀበለ ያለው ሕዝብ ወያኔን በሆነው መንገድ ሁሉ በቶሎ ማስወገድ ያሻል ባይ ነው። በወያኔ ላይ ሱዳን ተጨምሮ የሚያጠቃው ሕዝብ የትግል ያለህ እያለ ነው።የሀገር ውርደትና የሕዝብ መከፋፈል አደጋ ያሳሰበው ሁሉ የወያኔን አገዛዝ ውድቀት ይፈልጋል። ውድቀትና ውድመት እንጂ ድርድር፤መተቃቀፍና በምርጫ አማካይነት ዕድሜውን ማራዘምን አይደለም። ይህንን የሕዝብ ድምፅ ግን አወቅን ባዮቹ እያዳመጡት አይደሉም። የተናቀ ውሎ አድሮ እነ ዶክተርን እነ ጌቶችን ትምህርት መስጠቱ ግን አይቀርም። በትግሉ ሕዝብ ለውጥን ያዋልዳል፤ያስወልዳል። ሕዝብ ለውጥ በምርጫ የሚልን አቅዋም አንቅሮ ተፍቶታል፤አሽቀንጥሮ ጥሎታል። ከአስከፊው

ተመክሮ ተምሯል:: ችግሩ ያለው ከሕዝብ ሳይሆን ከድርጅት መሪዎች ነው:: ተጨባጩ ሁኔታና ሀቁ ደግሞ ከምርጫ ይልቅ ጡጫው ቡጢው ለወያኔ የሚገባው ቋንቋ ነው የሚል ነው:: በኢትዮ ጵያ ዛሬም ቢሆን የፖለቲካ ስልጣን ከምርጫ ሳጥን ውስጥ የለችም::የኢትዮጵያ ሕዝብ ከድርጅቶ ቹና መሪዎቹ የሚጠብቀው ለወያኔ መጎንበስን ወይም በወያኔ ምርጫ መግባትን ሳይሆን ብረት አንስቶ ወያኔን አምርሮ ታግሎ ማስወገድን ነው:: ምን አልክ ቢባል ሚሊዮኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ይላል:: የተመቻቸውና የፈራ፤ የራቁና አሜሪካ አባቴ ያሉ ግን ሌላ ሊሉ ቢችሉም:: ሕዝብ ን የናቁና ለሕዝብ አዋቂ ነን እኛ ነን ያሉ ደግሞ በሕዝብ ቦታና ስም የፈለጉትን ለማድረግ ወደ ኋላ አይሉም:: ሕዝብ ሳይመርጣቸው በሕዝብ ስም ወሳኝ ሆነው ይሰየማሉ:: በሕዝብ ስም ራሳቸ ው በራሳቸው ያውም በባዕድ ሀገር ተመራርጠው የስደት መንግስት መሰረትን መጣንልህም እስከ ማለት እነሆ ይደርሳሉ:: አደብ መግዛትና ልክን ማወቅ አልተፈጠረባቸውም:: አሊያም ስደቱ ሰለቸን ማለቱ ሲገባቸው እነሆ ነፃ ልናወጣህ መጣን ብለው ከሕዝብ ጠላት ይደራደራሉ:: ትጥቅ ትግልን ያወግዛሉ:: ሰለጠንን ብለው ለባዕድ ይጎነበሳሉ:: ድርጅቶችን አውግዘው ለተደራጀው ፈለጉም አልፈለጉም ድጋፍን ይለግሳሉ:: ሰበብ ደርድረው ከወያኔ ጫማ ስር ሲወድቁ ያው ሳይውል ሳያድር በሕዝብ ይጋለጡና ጠቅለው ተለጣፊ ይሆናሉ:: ምሳሌዎች ሞልተዋል:: ሁሉም ግን የሕዝባችን መድህን ሊሆኑ ቀርቶ ሌላ ችግር ሆነው ይገኛሉ::

የቤቱ መቃጠል ለትኋኑ በጀኝ ከሚል አጣብቂኝ ከመድረስ እንቆጠብ ዘንድ ከወዲሁ መዘጋጀት እንዳለብን ግልፅ ነው:: እንደ ሕዝብ ሀገራችንን የማዳን ሀላፊነት አለብን:: ወያኔ እስከቻለ ገዝቶ ሲሳነው በትኖን አናክሶን ወደ ክልሉ ሊጠቃለል እየተዘጋጀ መሆኑ መረሳት የለበትም:: የትግራይ ሕዝብ በዚህ በኩል የዳር ተመልካች ሳይሆን ከቀረው ሕዝብ ጋር ሆኖ በወያኔ መንጋ ላይ መነሳት አለበት:: የመለስ ቡድን " ልጆቻችን " የሚባል ሳይሆን ጠላታችን ተብሎ መወገዝ ያለበት መሆኑ መረሳት የለበትም:: ከዚህ ተያይዞ ደግሞ ወያኔ ካጠመደልን ፈንጂ ሁሉ ማምለጥ የምንች ለው የኢትዮጵያ ሀቀኛ ልጆችና ጠበቃዎች ጉልበት ሲኖራቸውና አፍራሽ ገንጣዮችን ሊቋቋሙ ሲችሉ ብቻ ነው:: ወያኔና መሰሎቹ ታጥቀዋል፤ ሰራዊት አላቸው:: ይህን መቋቋምና ማሸነፍ የሚቻለው በምለላና በልመና ሊሆን አይችልምና ከወዲሁ ጉልበትን መገንባት ማፈርጠም ያስፈ ልጋል:: ለዚህ ነው የትግሉንም ተግባራት ቅደም ተከተል ማወቅ ወሳኝ የሚሆነው:: በጠላትና ወዳጅ ማንነት ላይ ግልፅ እስከተሆነ ድረስ ቀጣይ ተልዕኮአችን ምን መሆን አለበት ሲባል ዋናው ና ተከታዩን በማደባለቅ ትግሉን ውጤት አልባ እንዳናደርገው መጠንቀቅ ይኖርብናል:: ታጠቅ ጎበዝ ሲባል የለም ምርጫ እንሳተፍ ዓይነቱ ውዥንብር ማለት ነው:: ትግሉ ይጠንከር ይፋፋም ሲባል ከወዲሁ ጋሪውን ከፈረሱ አስቀድሞ ያውም የስደት መንግስት እናቋቁምና ከወያኔ ጋር እንደራደር ብሎ ሰበካ:: ዜጎች ለሀገራችሁ ስርየት ራሳችሁ ተነሱ በራሳችሁ ተማመኑ ሲባል የለም የነገ ዕጣችንን ለአሜሪካ እንስጥና እነሱው ያድኑናል ብሎ በሬ ከአራጁን ማቀንቀን:: አዲሲቷን ኢትዮጵያ በዴሞክራሲና በሕዝብ እኩልነት ላይ እንገንባ ሲባል ዘረኝነትን ማራገብ፤ ወያኔን መምሰል፤ የግለሰብ አምባገነንነትን መመኘት መደናገርና ትግሉንም ማሽመድመድ ይሆናል:: የትግሉ ትኩረት ሕዝብን አስተባብሮ በወያኔ አገዛዝ ላይ ሁለገቡን ትግል ማፋፋምና

ወያኔን ለመጣል በቁርጠኛነት መነሳት ነው:: ከዚህ ሌላ ጨዋታ የአርበኛ ልጅ ይዋጋል፣ የአሮጌ ልጅ ያወጋልን ያመጣብናል::

ትግላችን በመሰረቱ ኢትዮጵያን ማዳን ቢሆንም ይህን ተልዕኮ ከዴሞክራሲ ለመነጠል መነሳቱ በጣም ስህተት ይሆናል:: የነገዪቷ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የሚሰፍንባት ካልሆነች ብዙሀኑን ለማቀ ፍና ለማታገል አይቻልም:: የሕዝብ እኩልነት ይረጋገጣል፣ ማንም አይረገጥም፣ መብት ይከበራል ካልተባለና በዚህ ላይ ስምምነት ካልተደረገ ነገ ከዛሬ በመሰረቱ አይለይም፣ ትላንትንም ሊደግም ይችላል የሚል ስጋት ካየለና ድምዳሜ ከተደረሰ በጋራ ተሰባስቦና ተደጋግፎ ለአንዲት ኢትዮጵያ የመታገሉ ጉዳይ ዳሽንን በእንብርክ ለመውጣት ያህል መሆኑ አይቀርም:: ስለዚህ ዴሞክራሲና ሀገር ማዳን የማይነጣጠሉ ግዳጆች ናቸው:: ጭፍን ዘረኞች ወይም ኢትዮጵያዊነትን የሚክዱ ለ ምሳሌ በሀገር አድኑ ትግል አብረው ሊሰለፉ መጠበቅ ከባድ ነው:: ይህ ስለተባለ ግን በርዕዮት ልዩነትና ዝርዝር እሰጥ አገባ ገብቶ መጠላለፉ ጠቃሚ ነው ማለት አይደለም:: መሰረታዊ ዴሞክ ራሲን መስማሚያ አድርጎ መነሳት ግን የሚቻልና የሚመረጥም ነው:: መለስተኛ ቅራኔ ዋና ሆኖ እንቅፋት እንዳይሆንም ማለት ነው::

በድርጅቶች ዘንድ ድክመቶችና ውዝንብሮች በመብዛታቸው ትኩረታችንን ወደነሱ አዙረን ወቀሳና ትችት የምናሰማው ታርመው ሚናቸውን ይወጡ ዘንድ በአዎንታዊ ፍላጎትና ስሜት እንጂ በአፍራሽነት አይደለም:: ትግሉ ይሳካ ዘንድ ድርጅቶች መኖራቸውና መጠናከራቸው ወሳኝና አስፈላጊ ነው:: የድርጅቶችን ድክምት ማጠየቂያ አድርገው ድርጅቶችን አውግዘውና አላስፈላጊ ናቸው ብለው ራሳቸውን በአዲስ ስብስብ መልክ ወይም በማህበርም ደረጃ ሊተኩ የሚጥሩት ያሰቡት ካለመሳካቱ ሌላ ለወያኔ እንጂ ለትግሉ አይጠቅሙም:: ከሁለገቡ ትግል አንፃር ሁሉም ሀገር ወዳድ ሚና የበኩሉን መስራት ሲኖርበት ዋናው ትኩረተ ግን ወያኔን በኃይል ማስወ ገዱ ላይ መሆን አለበትና በሀገር ውስጥም በውጭ ሀገርም ያለው ኢትዮጵያዊ በቅድሚያና በዋናነት በዚህ ትግል የተሰማሩትን ማገዝ፣መደገፍ፣ ማጠናከር አለበት::

እሾኽ በእሾኽ ይነቀሳል:: የታጠቀን የተደራጀን ኃይል ለማደባየት መደራጀት መታጠቅና አምርሮ መታገል ያስፈልጋል:: ነፃ ምርጫው ከድል በኋላ፣ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ከተረጋገጠ በኋላ:: ጋሪው ከፈረሱ አይቅደም-- ጉዞ ከታሰበ፣ ለውጥ ከታለመ ፣ከወያኔ መገላገል ከተፈለገ::